# ክልል አቀፍ ምዘናዎች፥
# የወላጅ/አሳዳጊ የተሳትፎ መመሪያ እና የእምቢታ መረጃ

ለሁሉም ተማሪዎች ከፍተኛ ጥራት ያለው ትምህርት ተደራሽ መሆኑን የእርስዎ ትምህርት ቤት እና ዲስትሪክቱ ማረጋገጥ እንዲያስችላቸው የእርስዎ ተማሪ በክልል አቀፍ ምዘናዎች ላይ መሳተፋቸው ጠቃሚ ነው።ቀደም ባሉ ጊዜያት፣ የአካል ጉድለት ያለባቸው ተማሪዎች እና የእንግሊዘኛ ተማሪዎች አብዛኛውን ጊዜ ከክልል አቀፍ ምዘናዎች የተገለሉ ነበሩ። ሁሉም ተማሪዎች ክልል አቀፍ ምዘናዎችን እንዲወስዱ በማድረግ፣ ትምህርት ቤቶች እና አስተማሪዎች ሁሉም ተማሪዎች ስላሉበት ሁኔታ የበለጠ መረጃ እንዲኖራቸው ያስችላቸዋል። ይህም ትምህርት ቤቶች የሚሰጡትን ትምህርት ያለማቋረጥ እንዲያሻሽሉ እና ተጨማሪ ድጋፍ የሚያስፈልጋቸውን ቡድኖች፣ ክፍሎች፣ ወይም የትምህርት አይነቶችን እንዲለዩ ያስችላቸዋል።

## ምዘናዎች ከመስፈርቶች ጋር ይገናኛሉ

ክልል አቀፍ ምዘናዎች የሚኒሶታ አካዳሚክ ደረጃዎች ወይም የ WIDA የእንግሊዘኛ ቋንቋ እድገት ደረጃዎች ላይ የተመሰረቱ ናቸው። እነዚህ ደረጃዎች በህዝብ እና የቻርተር ትምህርት ቤቶች ከመዋዕለ ህጻናት –12 ያሉ ተማሪዎች ሊማሩት የሚገባው እውቀት እና ክህሎትን ይገልጻሉ። ሚኒሶታ ከፍተኛ ጥራት ላለው ትምህርት ቅድሚያ ይሰጣል፣ እና ክልል አቀፍ ምዘናዎች አስተማሪዎች እና መሪዎች የተማሪን እና የትምህርት ቤት ስኬትን እንዲገመግሙ እድል ይሰጣሉ።

### የሚኒሶታ አጠቃላይ ምዘናዎች (MCA) እና የሚኒሶታ የአካዳሚክ ክህሎቶች ፈተና (MTAS)

MCA እና MTAS የሚኒሶታ ከመዋዕለ ህጻናት –12 የአካዳሚክ ደረጃዎችን የሚማር ተማሪን በአጭሩ የሚለኩ የንባብ፣ የሂሳብ እና የሳይንስ ዓመታዊ መመዘኛዎች ናቸው።

### ACCESS እና Alternate ACCESS ለእንግሊዘኛ ተማሪዎች

ACCESS እና Alternate ACCESS የተባሉት የእንግሊዘኛ ተማሪዎች ዓመታዊ መመዘኛዎች ሲሆኑ፥ WIDA የእንግሊዘኛ ቋንቋ የእድገት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግ የአዳሚክ እንግሊዘኛ ትምህርት ላይ ያላቸውን እድገት የሚመለከት መረጃ ይሰጣሉ።

## ክልል አቀፍ ምዘናዎች ቤተሰቦችን እና ተማሪዎችን ይረዳሉ

በክልል አቀፍ ምዘናዎች ላይ መሳተፍ ቤተሰቦች የተማሪያቸውን የትምህርት ሁኔታ አጭር እይታ እንዲያዩ  በትምህርት ቤት ለስኬታቸው እንዲሚገቱ ያግዛቸዋል። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተማሪዎች የ MCA ውጤቶችን መጠቀም ይችላሉ ለ፥

- በሚኒሶታ ስቴት ኮሌጅ ወይም ዩኒቨርስቲ ውስጥ ኮርስ እንዲወስዱ። ተማሪዎች ለኮሌጅ ዝግጁ የሚያደርግ ውጤት ካገኙ፣ ለዚያ ትምህርት የማካካሻ፣ ክሬዲት የሌለው ኮርስ መውሰድ አያስፈልጋቸውም።
- በትምህርት ቤቶች ፕሮግራሞች ውስጥ ለድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ምዝገባ አማራጮች (PSEO) እና ኮሌጅ።

ACCESS ወይም Alternate ACCESS የሚወስዱ የእንግሊዘኛ ተማሪዎች እና የተወሰኑ መስፈርቶችን የሚሉ ተማሪዎች ከእንግሊዘኛ ተማሪ ፕሮግራሞች የመውጣት እድል አላቸው።

## ክልል አቀፍ ምዘናዎችን መውሰድ ተማሪዎን በትምህርት ቤት ውስጥ ያግዛል

ክልል አቀፍ ምዘናዎች ሁሉም ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ ስለሚማሩት የትምህርት ይዘት ያላቸውን ተሳትፎን አስመልክቶ ለትምህርት ቤትዎ እና ዲስትሪክቱ መረጃ ይሰጣል። ይህ መረጃም ለሚከተሉት ያግዛል፥

- አስተማሪዎች የመማሪያ ሰነዶቻቸውን እንዲገመግሙ ያግዛል።
- ትምህርት ቤቶች እና ዲስትሪክቶች በቡድኖች መካከል ያለውን ኢፍትሃዊነትን እንዲለዩ፣ ዋና መንስኤዎችን እንዲለዩ እና ድጋፎችን እንዲሰጡ ያግዛል።

- የትምህርት ቤት እና የዲስትሪክት መሪዎች ሁሉንም ተማሪዎች ለመደገፍ ገንዘብ እና ግብዓቶችን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው ያግዛል።

## በክልል አቀፍ ምዘናዎች ላይ የተማሪ ተሳትፎ

አስፈላጊ በሆኑ የስቴት እና የአካባቢ ምዘናዎች ላይ የተማሪ ተሳትፎ የሚወሰነው በወላጅ/ሞግዚት ምርጫ ነው። ተማሪዎ በክልል አቀፍ ምዘና ላይ እንዳይሳተፉ ከመረጡ፣ እባክዎ ለውሳኔው ምክንያት የሆነውን በቅጹ ላይ ይጻፉ። የአካባቢ ምዘናዎችን በሚመለከት የበለጠ ለማወቅ የተማሪዎን ትምህርት ቤት ያግኙ።

## በክልል አቀፍ መመዘኛዎች ላይ ያለመሳተፍ ውጤቶች

- ተማሪው የግል ውጤት አያገኝም። ለ ACCESS እና Alternate ACCESS፣ ተማሪው ከእንግሊዘኛ ትምህርት ፕሮግራሙ የመውጣት እድል አይኖረውም።
- የትምህርት ቤት እና የዲስትሪክት ምዘና ውጤቶች ያልተሟሉ ይሆናሉ፣ ይህም የተማሪውን የትምህርት ሁኔታ ትክክለኛ ስዕል ለማግኘት የበለጠ አስቸጋሪ ያደርገዋል።
- የተወሰኑ ስሌቶች ላይ ባይሳተፉም እንኳን ሁሉም ብቁ የሆኑ ሁሉም ተማሪዎች የሚካተቱ በመሆኑ፣ የትምህርት ቤት እና የዲስትሪክት የተጠያቂነት ውጤት ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል። ይህም ትምህርት ቤቱ ድጋፍ ለማግኘት ወይም ለስኬቱ እውቅና የማግኘት ችሎታው ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል።

ባለመሳተፍ ምክንያት ሊከተሉ የሚችሉ ማንኛው ሌሎች ነገሮች ስለመኖራቸው ለማወቅ የአካባቢዎን ትምህርት ቤት ወይም ዲስትሪክት ጋር ያረጋግጡ።

ለበለጠ መረጃ የክልል አቀፍ የፈተና ገጽን ይመልከቱ

(education.mn.gov > Students and Families > Programs and Initiatives > Statewide Testing)

### ተጨማሪ መረጃ

- በአማካይ፣ ተማሪዎች በየዓመቱ ክልል አቀፍ ምዘናዎችን በመውሰድ የሚያጠፉት ጊዜ ከትምህርት ጊዜያቸው ከ1 ፐርሰንት በታች ነው።
- የሚኒሶታ ህጎች ተማሪዎች የዲስትሪክት ወይም የትምህርት ቤት ምዘናዎችን በመውሰድ የሚያጠፉት ጊዜ በየዓመቱ እንደ የክፍል ደረጃው እስከ 11 ሰዓታት ወይም ከዚያ ያነሰ እንዲሆን ገደብ አስቀምጠዋል።
- የትምህርት ቤት ዲስትሪክቶች እና የቻርተር ትምህርት ቤቶች በእያንዳንዱ የትምህርት ዓመት መጀመሪያ ላይ ምዘና የሚደረግበትን ጊዜ በድረገጻቸው ላይ እንዲለጥፉ ይገደዳሉ። ስለ ምዘናዎች የበለጠ መረጃ ለማግኘት የዲስትሪክትዎን ወይም የቻርተር ትምህርት ቤትዎን ድረገጽ ይመልከቱ።

(ማስታወሻ፡ ይህ ቅጽ ተግባራዊ የሚሆነው ለ 20____ እስከ 20_ የትምህርት ዓመት ብቻ ነው።)

DEPARTMENT OF EDUCATION

## የክልል አቀፍ ምዘና፡ የወላጅ/ሞግዚት ያለመሳተፍ ውሳኔ

ይህን ቅጽ በመሙላት፣ ተማሪዎ በክልል አቀፍ ምዘናዎች ላይ እንደማይሳተፉ እና ግላዊ የምዘና ውጤቶችን እንደማያገኙ እየገለጹ ነው።ይህ ቅጽ ተገቢው ፈተና ከመሰጠቱ በፊት ወደ ተማሪዎ ትምህርት ቤት መመለስ አለበት።

### የተማሪ መረጃ

የመጀመሪያ ስም፡ ______________________ የአባት ስም የመጀመሪያ ፊደል፡ ________________________________________
የአያት ስም፡ ___________________________

የትውልድ ቀን፡ ________/_____/________ በአሁን ወቅት ያለው የክፍል ደረጃ፡ ______

ትምህርት ቤት፡ _____________________________________________ ዲስትሪክት፡_____________________________________

የወላጅ/አሳዳጊ ስም (ይጻፉ)፡ _________________________________________________________________________________

የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ፥ ______________________________ ቀን፥ ______________

የእምቢታ ምክንያት፥

እባክዎ በዚህ የትምህርት ዓመት ተማሪው እንዳይሳተፍበት የመረጡት ክልል አቀፍ ምዘና(ዎች)ን ያመልክቱ፥

☐ MCA/MTAS ንባብ ☐ MCA/MTAS ሳይንስ

☐ MCA/MTAS ሂሳብ ☐ ACCESS/Alternate ACCESS

የአካባቢዎ ምዘናዎች ላይ አለመሳተፍን መምረጥ እንዴት እንደሚችሉ የበለጠ መረጃ ለማግኘት
ትምህርት ቤትዎን ወይም ዲስትሪክትዎን ያግኙ።